በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

# ክፍል አሥር

**በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**በሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን

- እውነተኛይቱ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በታሪካዊ ጉዞዋ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ በዓለም ያሉትን ሁሉ ስባ አቅፋ ይዛቸዋለች፡፡ በኃይል ላይም ኃይል እየጨመረች ከፍ ብላለች፡፡

- አሁን ከትምህርተ ሃይማኖትዋ፤ ቅዳሴዋ፤ ምልክትዋ፤ ቀኖናዋ፤ … ጋር ፍሬዋ የበዛ መልካም ዛፍ ሆናለች፡፡

- ክርስቶስ ብዙ አካል እንደሌለው ሁሉ ልትኖር የምትችለውም እውነተኛይቱ የርሱ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት፡፡

- እስካሁን እየከፈለ ወስዶ ከእውነተኛይቱ ለይቶ እያሳተ ብዙዎቹን የበተነው ጥንተ ጠላታችን ዲያቢሎስ ነው፡፡ #በእርሱም ዘንድ እውነት የለም፤ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ነው; ዮሐ 8፡44፡፡

- ሰይጣን ሐሰተኛ ሐሳቦችን ካስቀመጠ በኋላ ያን ሰው የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ሆኖ እንዲሰማው ያደርገዋል፡፡ ያም ሰው እንግዳ ትምህርቱን በቀናዒነትና ራሱንም መሥዋዕት በማድረግ ጭምር ማስፋፋት ይጀምራል፡፡ የሚሰራውም ሁሉ የክርስትናውን ሃይማኖት #ለማንጻት;፤ #ለማሻሻል; የሚያደርገው አድርጎ ያስባል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም እንግዳውን ትምህርት በእውነተናው ትምህርት የተነሣ ስትቃወም ክህደቱን የያዙት ሁሉ ተለይተዋት ክህደታቸውን ይዘው በጠላት መሪነት ይወጣሉ፤ እውነተኞች ነን በማለት አዲስ ቡድንም ይፈጥራሉ፡፡

## *እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን…*

- በዚህም መንገድ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ክህደቱ እየሰፋ ሄዷል፡፡ በመጀመሪያ አርዮሳውያን፤ በመቀጠልም የመቅዶንዮስና የንስጥሮስ ተከታዮች፤ እንዲሁም ካቶሊኮች ከእውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ተለይተው ወጥተዋል፡፡ ከነርሱም የተሐድሶ እንቅስቃሴ አራማጆች ፕሮቴስታንቶች ተፈጥረዋል፡፡ ተከትሎም የብዙዎች ቀንድ ከሆኑት ከነርሱ ቁጥራቸው የማይታወቅ ቡድኖች ተፈጥረዋል፡፡ እነዚህም ሁሉ ጥንት በቀደሙት አባቶቻችን ጉባኤያት የተወገዙ በአዳዲስ ቃላት ተቀብተው የቀረቡ የክህደት ትምህርቶች ድግግሞሾች ናቸው፡፡

- ሰይጣን በእውነተኛው የክርስቶስ ትምህርት በአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ጸንተው የሚኖሩትንም ቢሆን በመከፋፈል ወይም ዛሬ በውጪ ዓለማት እንደሚታየው በየአህጉሮቹና በየከተሞቹ በሚገኙ አጥቢያዎች መካከል ግጭት በመፍጠር ለመከፋፈል ይሞክራል፡፡ *ሮሜ 11፡20፤ 2ኛ ተሰ 3፡1-2፡፡*

- አሁን ያሉት እነዚህ ወይም እነዚያ… ሁኔታዎች መስተካከል አለባቸው በሚል የርስ በርስ ክርክሮች፡ ጭቅጭቆች እንዲበራከቱና በኋላም በመለያየት እንደ ማይተዋወቁ ባዕዳን እንዲተያዩ ለማድረግ ይሞክራል፡፡ አጀማመሩ ይኽን አናደርግም በሚል እንግዳ አካሄድን መተዋወቅ ወይም ማስተዋወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

- ታዲያ አንድ የዋህ አማኒ ይህን በመሰሉ ግራ የሚያጋቡ ሁኔታዎች መካከል መንገዱን በግልጽ እንዴት ሊመለከት ይችላል?

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን…

- ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን የማትከፈልና በማይበጠስም ትስስር የሐዋርያትን ትምህርት፤ ትውፊት በመከተል ከሐዋርያት ጀምሮ ከአንዱ ፓትርያርክ ወደ ሚቀጥለው ሳትቋረጥ የምትቀጥል መሆንዋን መረዳት ቀዳሚ ቁም ነገር ይሁን፡፡

- ይህችም ቤተ ክርስቲያን ታድጋለች ከዚህም ጋር አንድነትዋንና ማንነትዋን ጠብቃ ትኖራለች፡፡

- በሃይማኖት ጸሎትም #ከሁሉም በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሠሰበሰቧት በአንዲት ክብርት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡; በማለት የምንጸልየውም የሚያመለክተው አንዲት ሆና የምትሰጠውን አገልግሎትዋን፡- የሃይማኖትና የዶግማ፤ የቀኖናና የቅዳሴ አንድነትዋን ነው፡፡

- ይህችም ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ ነበረች፤ ዛሬም አለች እስከ ዓለም ፍጻሜ ትኖራለች፡፡ #በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፡፡; *ማቴ 16፡18፡፡*

- ስለዚህ የሚሻለው የሳቱት፤ የወጡት፤ የወደቁት ሁሉ ወደዚህች አንዲቱ ቤተ ክርስቲያን ቢመለሱ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በሰው የምትቋቋም ድርጅት ሳትሆን የክርስቶስ አካል ናት፡፡ *#ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው፡፡ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት፡፡;* *ኤፌ 1፡23፤ ሥራ 20፡28፡፡*

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን...

- ሰውን በማኅበራዊም ይሁን በሌሎች መንገዶች ማቀራረብ ማግባባት የሚገባ ቢሆንም ይኽ ተወስዶ እውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን በክህደት ከወጡት ጋር በድፍን ማዋሐድ ግን በእግዚአብሔር አልተፈቀደም።

- ይኽን በተመለከተ የሚሻለው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ትምህርቷን ያለ ምንም ማጓድል፡ ተጨማሪ ነገር ወይም ዘመናዊ ተቃራኒ አስተሳሰብ እንዳለ ተቀብሎ መመለስ ነው።

- ክርስቶስ ብዙ #አካሎች; የሉትም፤ እንደዚሁም በርካታ እውነተኛ አብያተ ክርስቲያናት ሊኖሩ አይችሉም። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን የማትከፈል የክርስቶስ አንዲት አካል ናትና። *ኤፌ 1፡23፤ የሐዋ. ሥራ 20፡28፤ ኤፌ 4፡5።*

- ስለዚህ እውነተኛይቱ በቴ ክርስቲያን እስካሁን አልተከፈለችም ወደፊትም አትከፈልም ነገር ግን የከሃድያኑ ክህደትና ከእውነተናይቱ ቤተክርስቲያን እየተነጠሉ መውጣት የነበረ ነው አሁንም አለ እስከ ዓለም ፍጻሜም ይኖራል። *#ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ።*; *1ኛ ዮሐ 2፡19።*

- ይህንንም በተመለከተ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና ክደው የወጡት በንስሐ እስኪመለሱ ድረስ ከነርሱ ጋር በጸሎትም ሆነ በምስጢራተ ቤተክርስቲያን አብሮ መሳተፍን ይከለክላል።

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን…

- ማንኛውም ሰው እውነትንም ሆነ መዳንን የክርስቶስ አካል ከሆነች ከእውነተኛይቱ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያገኛል፡፡ እግዚአብሔርን በእውነት የሚወዱት ሁሉ ከእርሱ ጋር ፈጽሞ ተዋሕደው መኖርን ይፈልጋሉ፡፡ ክርስትናም የሚገኘው በዚኽ ፍቅር ውስጥ ነው፡፡

- ክርስቶስን የሚወድዱት ሁሉ በዚሁ ፍቅር ወደ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ፍቅር ይሳባሉ፡፡*1ኛ ጴጥ 5፡9፤ 1ኛ ቆሮ 16፡13፤ 1ኛ ቆሮ 16፡5፤ ፊል 1፡27፤ ቆላ 2፡7፤ 2ኛ ጢሞ 4፡7፤ ይሁዳ 1፡3፡፡*

- ከዚህች ቤተ ክርስቲያን በፈቃዳቸው የወጡትንም በተመለከተ #የፊተኛውንም እምነታቸውን ስለ ናቁ ይፈረድባቸዋል; *1ኛ ጢሞ 5፡12፡፡* በማለት ቅዱስ መጽሐፍ ከፍርድ ራሳቸውን በንስሐ እንዲታደጉ ወይም እንዲያድኑ ያሳስባል፡፡

- *2ኛ ጢሞ 2፡18፤ 2ኛ ጢሞ 3፡8፤ ያዕ 2፡1፤ ያዕ 2፡14፤ የሐ ሥራ 14፡21-22፤ 1ኛ ጢሞ 4፡1-2፤ 1ኛ ጢሞ 6፡10* ይነበቡ፡፡

# ማጠቃለያ

## ማጠቃለያ

- ጌታችን ከኃጢአት ለይቶ ወደ ማዳኑ የጠራን በራሱ በምትመራው በታላቋ ቤተ ክርስቲያን መርከብነት ነው፡፡

- በሦስትነቱ የከበረ አንድ እግዚአብሔር አለ፤ እርሱም እውነቱ አንዲት ናት፡፡ አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለ ቤተ ክርስቲያኑም አንዲት ናት፡፡

- ጌታችንም በዚህች ቤተክርስቲያን የሚገኙትን ሁሉ የሚከተለውን ብሏል፡-
  - #አንተ ታናሽ መንጋ፥ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ፡፡; ሉቃ 12፡32፤
  - #በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ፡፡ በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ፡፡; ዮሐ 16፡33፤

# ማጠቃለያ...

- #ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ፥ በአንተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድህምና። እነሆ፥ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ፥ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ። የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።; ራእይ 3፡8-10

- በዚህ በምድር በምንመራው ጊዜያዊ ሕይወታችን ዋናው ነገር እውነትን - ከቤተ ክርስቲያኑ የማይለየውን ክርስቶስ እግዚአብሔርን አጥብቀን መያዝ ነው። #እናንተ እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል; ዮሐ 8፡32።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።